የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

ሳይቃጠል በቅጠል፣

ዛሬ "ሳይቃጠል በቅጠል" የሚለውን የአበው የአነጋገር ዘይቤ ለመጠቀም የሚያስገድደን ሁኔታ በመከሰት ላይ መሆኑ ግልጽ ነው። እያየን እንዳላየነው ሆነን ለማለፍ መሞከር የሚያስከፍለን ዋጋ አገርን እስከ ማፈራረስ የመድረስ አደምታ እንዳለውም እንገነዘባለን። በመሆኑም፣ ሳይቃጠል በቅጠል እያልን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለሰላም እንዲሰራ ጥሪ ለማቅረብ እንገደዳለን።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት)፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን ሰላማዊ ለውጥ እንደግፋለን ብቻ ሳይሆን የተጀመረው ለውጥ የታለመለትን ግብ እንዲመታ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማበርከት በሰላምና በሕጋዊ መንገድ ለመታገል የድርጅታችን አመራር አገር ቤት ገብቷል፣ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴም ጀምሯል። በዚህ ሂደት ውስጥ እየታዘብናቸው ያሉ አስፈሪና አደገኛ ክስተቶች በዝምታ መታለፍ እንደሌለባቸውም እናምናለን።

ህዝባችን ዕድሜውን በመላ ሲታገልለትና ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈለበትና እየከፈለበትም ያለው የለውጥ ጅማሮ ጥልቀት ኖሮት ህዝባችን ወደሚመኘው ከፍታ ለማድረስ የሚደረገውን ጥረት ተገቢ ባልሆነና ከሕግ-ውጭ በሆነ አሰራር እንዳይቀለበስ ስጋት አድሮብናል። ስለሆነም፣ ለዚህ ለውጥ ደንቃራ የሚሆኑትን ክስተቶች መመከት የእያንዳንዱ ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊን የሚመለከት ጉዳይ ነው። በዚህ በኩልም ድርጅታችን የበኩሉን ገንቢ ሚና ለመወጣት ዝግጁ ነው።

ይህንን ካልን ዘንዳ፣ አሁን በትግራይና አማራ ክልሎች መካከል እየተከሰተ ያለው በተለይም በሁለቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች፣ ህወሓትና ብአዴን መካከል የተከሰተውን የፖለቲካ ቁርቁስ በድንበር ጥያቄ እየተሳበበ እየጋመ እየሄደ መሆኑን እየታዘብን ነው። ለዚህም ሁለቱ ድርጅቶች በየበኩላቸው የብሔር ስሜትን በመቀስቀሻነት በመጠቀም ህዝብን ከህዝብ ጋር ለማጋጨት እየወሰዱት ያሉት እርምጃ በጊዜ ሊኮነን ይገባል፣ ት.ዴ.ትም ይህንን ሓላፊነት የጎደለውን እንቅስቃሴ አጥብቆ ይኮንናል።

በመሠረቱ ት.ዴ.ት ይህንን የዘር አከላለል ከመነሻው ስህተት እንደነበርና አሁንም አዲስ ዓይነት አወቃቀር ያስፈልጋል ብሎ በጽኑ ያምናል። ሆኖም፣ ዛሬ የድንበር ጥያቄን የሚያነሳው ብአዴን ከጫቱ ከጥንስሱ ጀምሮ ተስማምቶ ተቀብሎ ያጸደቀውና በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ እንዲካተት ወዶ የፈቀደ ድርጅት መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው። ያም ሆኖ በሂደት ሓሳቡን ቢቀይር እንኳን፣ ያንን ለማስፈጸም በዘር ማጽዳትና የአንድ አገር ህዝብን አላስፈላጊ ጦርነት ውስጥ ከትቶ ማፋጀት በፍጹም መሆን የሌለበት ነው። አካሄዱም ከትግራይ ክልል ድንበር በማስመለስ የሚቋጭ አይሆንም። የድንበር ጥያቄውም ቢሆን በህወሓትና ብአዴን ብቻም ተወስኖ የሚቀር አይሆንም። ስለሆነም፣ አካሄዱ ለአገራችን የሚተርፍ አደጋ አለው። ባንድ አገራዊ የካርታ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የአንድ አገር ዜጎች ህግና መንግሥት ባለበት ሁኔታ፣ በድንበር ይገባኛል ምክንያት ጦርነት ውስጥ መግባት ፍጹም ሓላፊነት የጎደለው ተግባር ነው።

በኢትዮጵያ፣ የውስጥ አስተዳደራዊ አከላለል ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየ ክስተት አለመሆኑ ደግሞ መታወቅ ይኖርበታል። በአፄ ሚኒሊክ፣ በአጼ ኃይለሥላሴ፣ በመንግሥቱ ኃይለማርያም ደርግና ዛሬም በኢህአዴግ ዘመነ

መንግሥታት እንዳመቻቸው ሲቀያይሩትና ሲያዋቅሩት ኖረዋል። በዚህ ምክንያት ጦርነት የተነሳበት ዘመን ግን ከዚህ በፊት አልነበረም፣ አሁንም መኖር የለበትም። በነዚህ ወንድማማች የአንድ አገር ህዝቦች መካከል እሳት እንዲነሳ በመጫር ላይ ያለ ክብሪት በጊዜ ሃይ ካልተባለ፣ የሚያስከትለው አደጋ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ በሚደርሰው እልቂትና ጥፋት ብቻ የሚወሰን አይሆንም። ወይም ደግሞ በውታና ግጦሽ እጥረት ምክንያት በአርብቶ አደሩ ህዝባችን መካከል የሚከሰተው መጥፎ አደጋ ዓይነት አይደለም፣ አይሆንምም። ይህ ቅዠት አሁን በምንታዘበው ሁኔታ ከቀጠለ ወይም እንዲቀጥል ከተተወ፣ አገርን የሚበታትን፣ ሕግና ሥርዓትን የሚያሳጣን ይሆናል።

ስለሆነም፣ ይህ ጉዳይ በዚህ እንዲቀጥል መፍቀድ የለብንም። ድንበር እየተባለ እንደ ሰበብ እየተስተጋባ ያለው አጀንዳም ቢሆን በጦርነት እንደማይፈታ ግልጽ መሆን አለበት። ይህ ድንበር እየተባለ ያለው ቦታ ዝም ብሎ ሰው የማይኖርበት ጠፍ መሬት ሳይሆን፣ ሰዎች ነዋሪዎች ያሉበት ቦታ መሆኑ መታወቅ አለበት። እነዚህ ነዋሪዎች ደግሞ ዱዳ ሳይሆኑ ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ መብቱ ከተሰጣቸውም ፍላጎታቸውንም ሆነ ማንነታቸውን ያለ ሓፍረት የመግለጽ ብቃት ያላቸው መሆኑ መታመን ይኖርበታል። የድንበር ቁርቁርስን አስገድዶ ለመፍታት፤ ኢትዮጵያዊያንን ከክልል ማስወጣት፣ በሆነም ባልሆነም እየወነጀሉ ማሰርና ማሰቃየት፣ ንብረታቸውን መውረርና ግድያ መቆም አለበት። የህዝብ ጠላት የሆነ ህዝብ ኖሮ አያውቅም፣ አይኖርምም። በህዝቦች መካከል ሰላምም ሆነ ቅራኔና ጦርነት እንዲከሰት ምክንያት የሚሆኑት ሁሌ ባንድም ይሁን በሌላ መልኩ፣ በግላጭም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቀሰቅሰው የፖለቲካው ኤሊት እንጂ ህዝብ ሆኖ አያውቅም። ስለሆነም፣ ህወሓትና ብአዴን እንደየተግባራቸው በነርሱ የተነሳ ለሚከተለው ጥፋት በሓላፊነት እንደሚጠየቁ ከወዲሁ ጠንቅቀው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል።

በተለይም፣ ባሁኑ ጊዜ በብአዴን በኩል እየታየ ያለው ዳተኝነት የሚያዝናናን ሆኖ አይታይም። በክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን ዘር ተኮር ጥቃት ለመቆጣጠር አልቻለም ወይም አልፈለገም ወይም ደግሞ አቅም አጥሮታል ብለን እንገምታለን። በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ የምንታዘባቸው ዘር ተኰር ጥቃቶችም አስነዋሪነታቸው ታውቆ ከመኮነን ባለፈ ሕጋዊ እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚያስፈልጉ እናምናለን።

ዛሬ ከመሃል አገር ወደ ትግራይ የሚጓዝ የግልም ሆኑ የመንግሥት ንብረቶች ወሎ ውስጥ በጠራራ ፀሃይ የሚካሄደው ዘረፋ ከተራ ውንብድና ተለይቶ የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር ይፈጸማል ተብሎም ለማሰብ የሚከብድ ሆኗል። የአማራ ክልል መንግሥት ይህንን ተግባር የማስቆምና መቆጣጠር አለመቻል፣ የችግሩን ጥልቀት ማሳያ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። አገራችንን ሊበታትን የሚችል አደገኛ ደወል መሆኑ ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት።

በመሆኑም፣ ይህ ችግር ይበልጥ ሳይባባስና አገራዊ ቀውስ የመሆን ደረጃ ሳይደርስ የፌደራል መንግሥቱ፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌደሬሽን ምክር ቤቶች ተገቢ እርምጃ እንዲወስዱ ት ዴ ት ጥሪውን ያቀርባል። መሆን የማይገባቸው ነገሮች ከሆኑ ብኋላ መቆጨቱ ትርጉም አይኖረውምና።

ህወሓትና ብአዴንም ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጩ ተግባራትን ከማከናወን እንዲቆጠቡ ት ዴ ት በጥብቅ ያስጠነቅቃል።

ከዚህም በተጨማሪም የትግራይ ክልላዊ መንግሥት አሁን በተጨባጭ ያለውን ሁኔታ አግባብ ላላቸው የፌደራል መንግሥት አካላትና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ እንዲያደርግ እንጠይቃለን። በተጨማሪም ህገደንቡን ተከትሎ ይህንን ጉዳይ ለመፍታት ያደረገው ጥረት ካለና እንቅፋት አጋጥሞት ከሆነም በግልጽ ለህዝብ እንዲያሳውቅ አጥብቀን እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ያገር ሽማግሌዎችም ይህንን በመከሰት ላይ ያለውን የድንበር ይገባኛል የጠብ ቅስቀሳ ለማስቆም የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ት ዴ ት ጥሪውን ያቀርባል!

ት ዴ ት

ጳጉሜ 2010 ዓ.ም.